DMU

**Advanced Journal of Interdisciplinary Studies 8(2024) 1381-1395**

Journal homepage: www.ajids.com.et

AJIDS

**Volume 8(2), Dec 2024**

# በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ፤ በልዑል አለማየሁ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተተኳሪነት

Sara Yohannes Zegeye[1], Amare Teshome Mulatu[2*]

[1]Report and Minutes Preparation Specialist, Office of the People's Representatives, Addis Abeba, Ethiopia

[2]Department of Ethiopian Language and Literature-Amaharic, University of Gondar, Gonder, Ethiopia

[*]Corresponding Author's email: amare.teshome47@gmail.com or Amare.Teshome@uog.edu.et

## አኅጽሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የባለሁለት ቡድን ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተናን መሰረት ያደረገ ከፊል ፍትነታዊ ስልትን ተከትሏል፡፡ ለጥናቱም ጎንደር ከተማ የሚገኘው ልዑል አለማየሁ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በአመቺ ንሞና ስልት ተመርጧል፡፡ በትምህርት ቤቱ በመማር ላይ ከሚገኙ አምስት ምድብ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በአንድ መምህር የሚማሩ 3 ምድብ ተማሪዎች በቀላል የዕጣ ንሞና ስልት ተለይተው ቅድመ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ከሶስቱ ምድቦች ተመጣጣኝ አማካይ ውጤቶች ያስመዘገቡ ሁለት ምድቦች ተለይተው በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ አንዱ የሙከራ፣ ሌላኛው የቁጥጥር ቡድን በመሆን በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በመቀጠል የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ በማስተማር ዘዴ፣ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በክፍል ደረጃው በሚጠይቀው መደበኛ ሥርዐተትምህርት መሠረት የማንበብ ክሂል ትምህርት ለ5 ሳምንታት ተምረዋል፡፡ በጥናቱም ቅድመ እና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመሆን አገልግለዋል፡፡ የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተናው ዓላማ ከልምምዱ በፊት በተማሪዎች መካከል ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መኖር-አለመኖሩን ለመፈተሽ ነው፡፡ በሌላ መልኩ የድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናው ዓላማ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የማንበብ ክሂልን ከተማሩ በኋላ፣ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት መኖር-አለመኖሩን ለመፈተሽ ነው፡፡ በቅድመ እና በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና የተገኙ ውጤቶችም በባዕድ ናሙና ቲቴስት የመተንተኛ ዘዴ ተሰልተዋል፡፡ የተገኙት ውጤቶች እንደሚያመላክቱት በሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ተቀራራቢ አማካይ ውጤቶች በመመዝገባቸው የተነሳ፣ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም በድህረ ትምህርት አንብቦ*

*የመረዳት ፈተና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ጉልህ ልዩነት (ቲ(97) =2.05 P=0.043) አሳይተዋል፡፡ ይህም የተገኘው ውጤት የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው አመላክቷል፡፡ ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ በጥናቱ መጨረሻ ክፍል ማጠቃለያ እና አስተያየት እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡*

***ቁልፍ ቃላት፡-** የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች፣ አንብቦ መረዳት፣ በግልጽ ማስተማር*

**Abstract**

*The main objective of this study is to examine the effect of explicit text structure strategies instruction on students' reading comprehension skill. The study followed a two-group pre-post quasi-experimental research design. Li'ul Alemayehu Primary School in Gondar City was chosen through a convenience sampling technique. Out of 5 groups of 7th grade students studying in the school, 3 groups of students taught by one teacher were selected and participated in the pre-test.Among the three sections of students who scored close to the average score in the pre-test, two sections were identified, and they were made to participate in the main study as an experimental group and the other as a control group. Subsequently, the experimental group students were taught reading skills through the explicit text-structure strategies instruction, while the control group students were taught reading skills according to the standard curriculum required by the grade level for 5 weeks. In the study, pre- and post-reading comprehension tests were used as data collection instruments. The pre-test aimed to assess whether students had equivalent reading comprehension abilities before the intervention. On the other hand, the purpose of the post-reading comprehension test was to examine whether there was a significant difference between the experimental and control group students after they learned reading skills using different teaching methods. The results obtained from the pre- and post-reading comprehension tests were also analyzed using the independent sample t-test. The results indicated that there was no significant difference between the two groups based on pre-test scores. However, in the post-reading comprehension test, the experimental group students showed a significant difference from the control group students (t (97) = 2.05, p = 0.043). This result indicates that explicit text structure strategies instruction has a significant effect on improving students' reading comprehension skill. Based on the results, the conclusion and recommendation are presented in the final section of the study.*

**Key words**: *Text structure strategies, Reading comprehension, Explicit instruction.*

## 1. መግቢያ

**የቋንቋ መማር ብልሃቶች ላይ ጥናት ማድረግ የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1960ዎቹ ዘመን ነው፡፡ በተለይም ግንዛቤያዊ ሳይኮሎጂ ከፍተኛ ትኩረት ባገኘበት ጊዜ የመማር ብልሃቶች ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር ልዩ ልዩ ብልሃቶች እንዲተዋወቁ ምክንያት ሆኗል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜም** Carton (1966) **የውጭ ቋንቋን ከማስተማር አኳያ ብልሃቶች ላይ ጥናት አድርገዋል** (Wiliams and Burden, 1997)፡፡ **በመቀጠል** Rubin (1975) **ከተለያዩ ምልከታዎች በመነሳት ተማሪዎች**

የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች በዝርዝር አሳይተዋል፡፡ ከRubin (1975) ጥናት በኋላ፣ ብልሃቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ በርካታ ጥናቶች (Brown, 1994; O'Malley & Chamot, 1990; Oxford, 1990) በተለያዩ ጊዜያት ተካሂደው ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

የቋንቋ መማር ብልሃቶች፣ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ወቅት የሚገጥሟቸውን ማናቸውም ችግሮች ለመቅረፍ፣ የትምህርት ሂደቱን ለማቅለል፣ ለማቀላጠፍና ለመረዳት ይሁነኝ ብለው በራስ ፍላጎት የሚመርጧቸው የመማር ልዩ ልዩ ዘዴዎች ናቸው (O'Malley & Chamot, 1990)፡፡ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ሂደቱን ፈጣን፣ አዝናኝ፣ ቀላል፣ ወደ ሌሎች ዘዴዎች ለመሸጋገር የሚከናወኑ ተግባራት እና የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ናቸው (Oxford, 1990)፡፡ በሌላ መልኩ O'Malley and Chamot (1990) ልዩ ልዩ ትምህርቶችን ወይም ባህሪያትን እያንዳንዱ ተማሪ በራሱ ለመረዳት፣ ለመማር እንዲሁም የተገኘ አዲስ መረጃን ይዞ ለመቆየት የቋንቋ መማር ብልሃቶች አስተዋጽኦቸው የላቀ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከላይ የተነሱ ሀሳቦችን Vann and Abraham (1990) እንደሚያጠናክሩት ውጤታማ ተማሪዎች በቋንቋ መማር ሂደታቸው ላይ ተመስርተው ተገቢውን የመማር ብልሃቶች መርጠው ይጠቀማሉ፡፡ ደካማ ተማሪዎች ግን ብልሃቶች ለመጠቀም ዝግጁ ባለመሆናቸው የተነሳ፣ ከመማር ብልሃቶች አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ሁነቶችን መረዳት ይከብዳቸዋል፡፡

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተግባር ላይ እየዋሉ ከሚገኙ ብልሃቶች መካከል የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች ይጠቀሳሉ፡፡ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች በ1975 ሜይር በተባሉ ምሁር እንደተዋወቁ ይነገራል፡፡ ሜይር እስከ 1980ዎቹ መጀመሪያ ድረስ ከመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስከ መካከለኛ የኮሌጅ ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃት አጠቃቀምና ተጽዕኖን በሚመለከት በርካታ ጥናቶች አድርገዋል (Meyer, 1975; Meyer & Rice, 1982)፡፡ በመቀጠል ከ1980ዎቹ በኋላ Meyer et al. (1980) የጽሑፍ ውቅር ብልሃትን በማስፋፋትና አስፈላጊ የሆኑ ሀሳቦችን በመምረጥ ጥሩ አንባቢዎች በጽሑፍ ውስጥ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በጥናታቸው ለማሳየት ችለዋል፡፡ ከ1990 በኋላ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን ተማሪዎች ለይተው እንዲያውቁና እንዲጠቀሙ በሚል እሳቤ ሙሉ ለሙሉ ወደመማር ማስተማር ሂደት ተሸጋግሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከ2000 ጀምሮ የጽሑፍ ውቅር ብልሃት በአንብቦ መረዳት ትምህርት ውስጥ ውጤታማነቱ ምን ያህል ነው? በሚል መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ትኩረት ያደረገ ጥናትና ምርምር ፍትነታዊ በሆነ መልኩ መዘጋጀት ጀምሯል (Meyer, & Ray, 2011)፡፡ ይህም እሳቤ እስከ አሁን ድረስ ተጠናክሮ በመቀጠል የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን ከማንበብ ትምህርት ጋር በማገናኘት ውጤታማነታቸውን በመፈተሽ ከጊዜ ወደጊዜ ከፍተኛ ትኩረት ሊያገኝ ችሏል፡፡

የጽሑፍ ውቅር፣ በውስጡ ዝርዝር ንዑሳን ብልሃቶች ያካተተ ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል የማወዳደር/ማነጻጸር (በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ጽንሰ ሀሳቦችን ተመሳሳይነት እና ልዩነት ላይ በማተኮር ጽሑፍን ማንበብ)፣ ምክንያት/ውጤት (በሁለት ሁነቶች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን መፈተሽ)፣ ችግር/መፍትሄ (በጽሑፍ ውስጥ ጥያቄ የሚፈጥሩ ወይም መፍትሄ የሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ በማተኮር

የመፍትሄ አካል ለመሆን ጥረት ማድረግ ) እና ቅደም ተከል ማደራጀት (በጽሑፉ ውስጥ ያሉ ዝርዝር ክስተቶችን ቅደም ተከተል በማስያዝ ከምን ጀምሮ የት ደረሰ? የሚለው ላይ ትኩረቱ ማድረግ) የሚጠቀሱ ናቸው (Amiria et al., 2012)፡፡ የጽሑፍ ውቅር ብልሃት ለቋንቋ ትምህርት መማር ማስተማር ከሚያበረክተው ፋይዳ አኳያ በምሁራን መካከል ክርክሮች ተካሂደዋል፡፡ የመጀመሪያው ምንም እንኳን የብልሃቶች ተቀዳሚ ዓላማ የቋንቋ መማርን ማቀላጠፍ እና ቋንቋን ለመማር ዓይነተኛ መሳሪያ /ዘዴ/ በመሆናቸው ትኩረት ተሰጥቷቸው የነበሩ ቢሆንም፣ ካላቸው የቋንቋ ጥናቶች ታሪክ አኳያ በብልሃቶቹ እና በቋንቋ መማር ውጤታማነት መካከል ስላለው ግንኙነት ያሳዩት ውጤት አወዛጋቢ መሆኑ ተጠቃሽ ነው (Piyanukool 2001)፡፡ በተመሳሳይ በ1990ዎቹ የተካሄዱት ምርምሮች ስለቋንቋ መማር ብልሃቶች ለመረጃ መሰብሰቢያነት በተጠቀሟቸው መሳሪያዎች ላይ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችን ማየት ተችሏል፡፡ ሁለተኛው በዘርፉ ላይ ጉልህ መከራከሪያ ነጥብ የነበረው ስለብልሃቶች ከተሰጡ ብያኔዎች እና ፅንሰሀሳቦች ጋር የተያያዘ ነው (Rose, 2012)፡፡ የዘርፉ ተመራማሪ ከሆኑት አንዱ (Rose, 2012) በወቅቱ አወዛጋቢ ወይም አከራካሪ የነበሩት ጉዳዮች እና ስምምነት ያላገኙት፤ ብልሃቶች የሚገኙት በአእምሮ ውስጥ ነው? ከአእምሮ ውጭ ነው? የተማሪ ብልሃቶች የሚያካትቱት እውቀትን፣ እሳቤን፣ ተግባርን ወይስ ሶስቱን ነው? ብልሃቶችን ለመመደብ /ለመፈረጅ/ በፅንሰ ሀሳብ? በቅደም ተከተል? ወይስ በጉድኝት ነው? ብልሃቶች የሚኖሩት በሁሉም የመማር ሁኔታዎች ነው? በተግባራትና በአውዶች ነው? ብልሃቶች በቋንቋ ሂደቶች ውስጥ ወሳኝ? ወይስ ተጨማሪ ነገሮች ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች አከራካሪ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

በሌላ መልኩ የጽሑፍ ውቅር ብልሃት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ መሰረታዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ምሁራን የተለያየ እይታ አላቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ውቅር ብልሃት በተወሰኑ የክፍል ደረጃዎች ላይ ይበልጥ ውጤታማ ሊሆን ይችላል የሚል ነው፡፡ የተለያዩ ተመራማሪዎች ስለ ጽሑፍ ውቅር ያላቸው ግንዛቤ ከዕድሜ ጋር እየጨመረ እንደሚሄድ በማስረዳት፣ በጽሑፍ መዋቅር ላይ የሚሰጠው ትምህርት በዕድሜ የገፉ ተማሪዎችን ከወጣቶች ይበልጥ ሊጠቅም እንደሚችል ያነሳሉ (Mayer et al., 1980; Englert & Thomas, 1987)፡፡ ይሁን እንጂ በቅርብ ጊዜ የተደረጉ ጥናቶች በመካከለኛ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል እንደሚረዱ በየጥናቶቻቸው አረጋግጠዋል (Williams et al., 2004; Williams & Pao, 2011)፡፡ ይህንንም ሀሳብ በማጠናከር Meyer and Ray (2011)፣ Armbuster et al. (1987)ን ዋቢ አድርገው በመማር ማስተማሩ ሂደት በአብዛኛው ተማሪዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ወደ ሁለተኛው እርከን ደረጃቸው እየጨመረ ሲሄድ አዳዲስ አወቃቀር ያላቸው ጽሑፎች ያጋጥሟቸዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ውስብስብ የጽሑፍ ዓይነቶች በጥልቀት መረዳት እንዲችሉ ቀድመው ከብልሃቶቹ ጋር መተዋወቅ እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ፡፡

ከማንበብ አላባዎች ውስጥ አንዱ አንብቦ መረዳት ነው፡፡ አንብቦ መረዳት ውስብስብ አዕምሯዊ ሂደት ሲሆን፣ አንባቢው የቀደመ እውቀቱንና ልምዱን መነሻ በማድረግ ጽሑፉን ትርጉም አዘል በሆነ መልኩ በጥልቀት ተገንዝቦ የማንበብ ተግባሩን

የሚወጣበት የክሂል ዘርፍ ነው (Ghafarpour, et al. 2013)፡፡ ማንበብ፣ ማንኛውንም ትምህርት ለመማር መሠረት ሲሆን፣ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማንበብ የቻሉ ተማሪዎች ለወደፊቱ የትምህርት ስኬታቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ነገር ግን በሀገራችን የማንበብ ክሂል እንዳልተሻሻለ የተለያዩ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ እንድሪስ (2009) እና ዘውዱ (2006) በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር እንደሚታይ በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡

በሌላ መልኩ በመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ላይ የተካሄደ የማንበብ ክሂል ግምገማ EGRA (2010) ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የፈተሸ ነው፡፡ በ2007 በአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው 14.6% የሚሆኑት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ብቁ ሆነው ሲገኙ፣ 33.7% ለደረጃው በሚመጥን የሚያነቡ እና ከደረጃ በታች የሚያነቡ ደግሞ 51.7% ተማሪዎች መሆናቸው ተገልጿል፡፡ በጥናቱ ውጤት እንደተገለፀው በኢትዮጵያ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ዝቅተኛ በመሆኑ ለቀላል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መልስ መስጠት የቻሉት ከ50% በታች የሚሆኑት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ የአማራ ክልል የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲታይ በአማርኛ አፍፈት የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ፊደል ለይተው ማንበብ የማይችሉት 27.5% የሚሆኑት ናቸው፡፡ በEGRA (2010) ጥናት ላይ የተገለፀው ሌላው ነጥብ እ.አ.አ በ2000፣ በ2004 እና በ2007 የተከናወኑት የጥናት ግኝቶች ያመላከቱት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ የሄደ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በማንበብ ክሂል ዙሪያ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ችግሩን ለመለወጥ መስራት ያስፈልጋል የሚል አስተያየት በጥናቱ መጠቆሙ ለዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

O’Malley and Chamot (1990) እና Oxford (1990) ብልሃቶች ከመምህሩ ሳይሆኑ፣ ከተማሪዎቹ የመጡ ዘዴዎች በመሆናቸው ተማሪዎቹ በሚፈልጉት መልኩ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ እድል ስለሚሰጣቸውና በመማር ማስተማር ሂደት የሚገጥሟቸውን ችግሮች እንዲፈቱ ስለሚያግዛቸው ለአንብቦ መረዳት ትምህርታቸው እንዲጠቀሙ ማበረታታት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም እሳቤ በመነሳት በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት ልዩ ልዩ ብልሃቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ ከፊል ፍትነታዊ እና በተዛምዷዊ ጥናቶች እየተካሄዱ ይገኛሉ (እንድሪስ፣ 2009; Amare, 2024; Lin, 2010) ፡፡ ለአብነት ያህል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ላይ ተመስርተው የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከፈተሹ ጥናቶች መካከል Amare (2024) እንደሚያስረዱት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት የማንበብ ብልሃቶች ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ከገለጹ በኋላ፣ብልሃቶቹ እንደመማሪያ ዘዴ በመሆን ስለሚያገለግሉ የተማሪዎች የቃላት ችሎታ እንዲጎለብት፣ የማንበብ ተነሳሽነታቸውና የማሰብ ክህሎታቸው እንዲሻሻል እንዲሁም በማንበብ ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመፍታት ስለሚያስችሉ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ለማጎልበት አስተዋጽኦ

አላቸው። ከዚህ በተጨማሪ Lin (2010) በጥናታቸው የተማሪዎቹ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ከደረጃው በታች ሊሆን ችሏል። በመሆኑም ልዩ ልዩ ብልሃቶች ላይ ትኩረት በማድረግ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ይገባል። የእነዚህም ጥናቶች ግኝት፣ ይህ ጥናት በማንበብ ብልሃት ላይ እንዲያተኩር ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል።

ከማንበብ ብልሃቶች ውስጥ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በጽሑፍ ውቅር ብልሃት ላይ ነው። ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት በብልሃቶቹ ላይ የተደረጉ ከፊል ፍትነታዊ ጥናቶች የተለያዩ ውጤቶች ማሳየታቸው እና በምሁራን ዘንድ በርካታ ክርክሮች እየተደረገባቸው የሚገኙ ብልሃቶች በመሆናቸው የተነሳ ነው። ለአብነት ያህል Amiria et al. (2012) የጽሑፍ ውቅር ብልሃት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ፈትሸዋል። በጥናቱም ሁለት የሙከራ ቡድኖችን በመውሰድ ለአንዱ ቡድን በማወዳደር/ማነጻጸር ብልሃት ለሌላኛው ቡድን በምክንያት/ውጤት ብልሃት የማንበብ ክሂልን እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ፣ በመጨረሻም በድህረ ፈተናው በማወዳደር/በማነጻጸር ብልሃት የተማሩ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው እንደተሻሻለ የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ተመስርተው የጽሑፍ ውቅር ብልሃትን በሙከራዊ ጥናት መልክ ከፈተሹ ጥናቶች ውስጥ የእንድሪስ (2009) ጥናት ተጠቃሽ ነው። ጥናቱም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሲሆን፣ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት፣ የማንበብ ግለብቃት እምነት፣ የማንበብ ተነሳሽነት እና የማንበብ ትኩረት ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ በጥናታቸው አመላክተዋል። የጥናቱን ውጤት መሰረት አድርገው በሌሎች የክፍል ደረጃዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በሚመለከት ጥናት ቢደረግ ስለብልሃቶች ሚና ያለውን ግንዛቤ ማስፋት እንደሚያስችል ጠቁመዋል።

ሙሉገበያ (2009) በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአንድ ቡድን በሁለት የጽሑፍ ውቅሮች ብቻ አተኩረተው ጥናት አድርገዋል። በጥናት ውጤታቸው የአንብቦ መረዳት ትምህርት የጽሑፍ አወቃቀርን መሰረት አድርጎ ቢቀርብ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንደሚጎለብት የጥናታቸው ግኝት ያመለክታል። ይህም ጥናት ከጽሑፍ አወቃቀሮች ውስጥ በምክንያትና ውጤት እና በገለጻ ላይ ማተኮሩ እና በአንድ ቡድን መጠናቱ ውስንነት ታይቶበታል። ስለሆነም ሌሎች አጥኚዎች ሁሉንም የጽሑፍ አወቃቀር አይነቶች አካተው ቢያጠኑ የተሻለ ግንዛቤ ሊገኝ እንደሚችል መጠቆማቸው ጥናቱን ለማካሄድ አነሳሽ ምክንያት ሆኗል። ከዚህ በተጨማሪ ጥሩነሽ (2005) በሰሜን ሸዋ ዞን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በአንድ ቡድን በሁለት የቴክስት ውቅሮች ብቻ የተካሄደ ጥናት ነው። በጥናቱ ውጤት መሰረት የጽሑፍ አወቃቀርን በቀጥታ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ፍላጎት ለማሳደግ ጠቃሚ መሆኑን ገልጸዋል። ነገር ግን ጥናቱ ከጽሑፍ ውቅሮች መካከል በችግርና መፍትሄ እና በማወዳደር ወይም ማነጻጸር ላይ ብቻ ማተኮሩ ጥናቱ ውስንነት እንዳለበት ገልጸዋል።

በሌላ በኩል Piyanukool (2001) የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች ለማንበብ ትምህርት ያለውን ውጤታማነት መርምረዋል፡፡ ጥናቱም በታይላንድ የኮሌጅ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሲሆን፣ እንግሊዝኛ ቋንቋን እንደዋና የትምህርት መስክ እየተማሩ ያሉ 126 ተማሪዎች ተሳተፈውበታል፡፡ ከፊል ፍትነታዊ ጥናቱ ለ10 ሳምንት ከተካሄደ በኋላ፣ የተገኘው የጥናት ውጤት እንዳመላከተው የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች አሁን ላይ ማንበብን ለማስተማር ተግባር ላይ ከዋለው ዘዴ አንብቦ መረዳት ችሎታን ከማሻሻል አኳያ የተለየ አስተዋጽኦ እንደሌላቸው ነው፡፡ በተመሳሳይ Ghafarpour et al. (2013) የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታዎች በሚጠይቁ ደረጃዎች ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ፈትሸዋል፡፡ በጥናቱም 30 ተማሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች የተማሪዎችን የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚጠይቁ ደረጃዎች ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሌላቸው በጥናታቸው ጠቁመዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Adugnaw and Birhanu (2024) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት የማንበብ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ፈትሸዋል፡፡ ጥናቱም ደብረ ታቦር ከተማ በሚገኘው ጣይቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ነው፡፡ ከጥናቱ ከተገኘው ውጤት በመነሳት፣ በማንበብ ትምህርት አውድ ውስጥ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማሻሻል ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሌለው ጠቁመዋል፡፡

በአጠቃላይ በተለያዩ ምሁራን የተጠኑት ጥናቶች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ያጎለብታሉ/አያጎለብቱም የሚሉ የውጤት ልዩነቶች ታይቶባቸዋል፡፡ ይህም የውጤት ልዩነት መኖር ለዚህ ጥናት እንደአነሳሽ ምክንያት በመሆን አገልግሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ቀጣይ ጥናት እንዲጠና በተመራማሪዎች መገለጹ (እንድሪስ፣ 2009)፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ የተጠኑ ጥናቶችም በተወሰኑ የጽሑፍ ወቅር ብልሃቶች ላይ ማተኮራቸውና የአብዛኞቹ የጥናት ንድፍ የባለአንድ ቡድን ሙከራዊ ጥናት መሆናቸው (ሙሉገበያ 2009፣ ጥሩነሽ 2005) ይህን ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አራቱ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች (የማወዳደር/ማነጻጸር፣ ምክንያት/ውጤት፣ ችግር/መፍትሄ እና ማደራጀት) ላይ ትኩረት በማድረግ፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል አስተዋጽኦ አለውን? ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ይህ ጥናት ምላሽ ሰጥቷል፡፡

## 2. የጥናቱ ዘዴ

### 2.1 የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የባለሁለት ቡድን ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተናን መሰረት ያደረገ ከፊል ፍትነታዊ ስልትን ተግባራዊ ሆኗል፡፡

### 2.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በጎንደር ከተማ ከሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች መካከል በልዑል አለማየሁ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ

በአመቺ ንሞና ዘዴ የተመረጠ ሲሆን፣ ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ከፊል ፍትነታዊ ጥናት ለማካሄድ የትምህርት ቤትን፣ የመምህራንን እና የተማሪዎችን ድጋፍ ማግኘት አስፈላጊ በመሆኑ የተነሳ አጥኚዎቹ እነዚህን ሁለንተናዊ ድጋፎች በትምህርት ቤቱ ማግኘት እንደሚችሉ በማሰባቸው ነው። እርከኑ እና የክፍል ደረጃው የተመረጠው በዓላማ ተኮር ንሞና ነው። የጽሑፍ ውቅር ብልሃት በማንበብ ትምህርት ውስጥ በየትኛው የክፍል ደረጃ ላይ መተግበር እንዳለበት በተለያዩ ምሁራን ዘንድ ክርክሮች ቢኖሩም፣ የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንዳመላከቱት ግን በመካከለኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ ቢተገበር ተማሪዎች በወደፊት የማንበብ ህይወታቸው እንዲጠቀሙበት ያስችላቸዋል ከሚሉት ጥናቶች (Williams et al., 2004; Williams & Pao, 2011) በመነሳት ይህ ጥናት በመካከለኛ የክፍል ደረጃ ላይ እንዲያተኩር ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም ከአምስተኛ እና ከስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ይልቅ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የተሻለ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ ስለታሰበ እና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ ክልል አቀፍ ፈተና የሚወስዱ በመሆኑ መረጃ ለመሰብሰብ የጊዜ እጥረት ይኖራል ተብሎ በመታሰቡ ምክንያት በዚህ የክፍል ደረጃ ላይ ሊተኮር ችሏል። ጥናቱ ከፊል ፍትነታዊ ስልትን የተከተለ በመሆኑ በአንድ መምህር ከሚማሩ የ7ኛ ክፍል 5 ምድብ ተማሪዎች መካከል ለ3 ምድብ ተማሪዎች የቅድመ ፈተና ተስጥቶ ተቀራራቢ አማካይ ውጤት፣ ያላቸው ሁለት ቡድኖች እንዲመረጡ ተደርጓል። ከሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል በተራ የእጣ ንሞና ስልት አንዱ የሙከራ፣ ሌላኛው የቁጥጥር ቡድን በመሆን በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል።

**2.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች**

በዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ ጥቅም ላይ የዋሉት ቅድመ እና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ናቸው። የቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናው ዋነኛ ዓላማ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማረጋገጥ ነበር። የድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናው ዓላማ ደግሞ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ከተማሩት የሙከራ ቡድን እና በተተግባሪው ዘዴ በተማሩት (የጽሑፍ ውቅር ብልሃትን በግልጽ ባልተማሩት) የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በየትኛው ዘዴ የተማሩት የተሻለ የአንብቦ መረዳት ውጤት እንዳስመዘገቡ ለመፈተሽ ነበር። ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ መርሃ ትምህርቱ ላይ የተመሰረቱና ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልትን የተከተሉ እንዲሆኑ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ለቅድመ እና ለድህረ ፈተናዎች የተዘጋጁት ምንባቦች ተመሳሳይ የቋንቋ አጠቃቀም ያላቸው፣ የተመጣጠነ የቃላት ብዛት የያዙና በአንድ ደራሲ የተጻፉ (ዘነበ ወላ "ልጅነት" ከሚለው ልቦልድ መጽሐፍ) ሁለት ምንባቦች ተመርጠዋል። ለእያንዳንዱ ቅድመ እና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አምስት እውነት /ሀሰት፣ አምስት ተቃራኒ ፍቺ የሚጠይቁ የአዛምድ ጥያቄዎች እና አስር የምርጫ ጥያቄዎች በአጠቃላይ ሀያ ጥያቄዎች ዝግ የአጠያየቅ ስልትን የተከተሉ ሆነው ተዘጋጅተዋል። ፈተናዎች ያላቸውን ተገቢነት ለማረጋገጥ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ሶስተኛ ድግሪ ባላቸው መምህራን ተገምግሞ ማስተካከያ ተደርጓል። በመቀጠል የፈተናውን አስተማማኝነት ለመለካት ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤት ውጭ በአዘዞ አጼ ፋሲል

አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በመማር ላይ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል በዕጣ ንሞና ስልት በተመረጡ አርባ ተማሪዎች በመምረጥ 20ዎቹ ቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናውን፣ 20ዎቹ ደግሞ ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናውን ተፈትነዋል። በመቀጠል ከአስተማማኝነት መለኪያ ዘዴዎች ውስጥ እኩል ክፋይ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። በዚህም መሰረት ቅድመ እና ድህረ ፈተና የተፈተኑ ተማሪዎች ከቀረቡላቸው የጥያቄዎች ብዛት በሙሉ ቁጥር እና በጎዶሎ ቁጥር ያስመዘገቧቸው ውጤቶችን በመመዝገብ በክሮንባኽ አልፋ ስሌት ከተሰሉ በኋላ፣ በቅድመ ፈተናው የተመዘገበው የክሮንባኸ አልፋ ውጤት 0.838 ሲሆን፣ በድህረ ፈተናው ደግሞ 0.724 ውጤት ሆኖ ተገኝቷል። እነዚህም የክሮንባኽ አልፋ ውጤቶች ከ0.7 በላይ በመሆናቸው ፈተናዎቹ አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል።

### 2.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ እና በድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ያስመዘገቧቸው ውጤቶች በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተዋል። ጉልህ ልዩነት ላሳየው ቡድን የዝምድና ጥንካሬውን ለመለየት የኮኸንስ ዲ ቀመር ስሌት ጥቅም ላይ ውሏል።

## 3. የአጠናን ሂደት

በቅድሚያ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች)ና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የትብብር ደብዳቤ ለተተኳሪ ትምህርት ቤቱ እንዲጻፍ ተደርጓል። በመቀጠል ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርና አስተዳደር አካላት ተሰጥቶ ፈቃደኝነታቸው ተጠይቋል። ፈቃደኝታቸው አወንታዊ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ፣ ለተተኳሪ ቡድኖች ቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል። ለተማሪዎችም የጥናቱን ዓላማ በማስገንዘብ ተሳታፊ እንዲሆኑ ፈቃደኝነታቸው ተጠይቆ ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ የስምምነት ውል ገብተዋል። በመቀጠል የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖቹን ለሚያስተምሩት መምህር የማስልጠኛ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ፣ በሙከራ ቡድኑ ለተሳተፉ ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች ምንነት፣ አይነቶችና በምንባብ ውስጥ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። በመቀጠል የክፍል ደረጃው በሚጠይቀው መደበኛ ሥርዐተትምህርት መሰረት በተዘጋጀው የማስተማሪያ ጽሑፍ የማንበብ ትምህርታቸውን በአራቱ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች (የማወዳደር/ማነጻጸር፣ ምክንያት/ውጤት፣ ችግር/መፍትሄ እና ቅደም ተከል ማደራጀት) ለአስር ክፍለጊዜያት ተከታትለዋል። በሌላ በኩል የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ለሙከራ ቡድኑ በተዘጋጁት የማስተማሪያ ጽሑፎች በተመሳሳይ ለ5 ሳምንታት እንዲማሩ ተደርጓል። ተማሪዎቹም ስለጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች ምንነት፣ አይነቶችና ተግባራቸው በግልጽ አልተማሩም፤ ስልጠናም አልተሰጣቸውም። ሆኖም በተተግባሪው ሥርዓተ ትምህርት ማለትም በቀጥታ የምንባቡን ርእስ አይተው በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በመወያየት፣ በማንበብ ጊዜና አንብቦ የመረዳት ተግባራትን እንዲሰሩና ያልተረዱትን እንዲጠይቁ በሚያስችል መልኩ ትምህርቱን ተምረዋል። በመጨረሻም ሁለቱም ቡድኖች ለአስር ክፍለጊዜያት ከተማሩ በኋላ ድህረ

ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ተፈትነዋል፡፡

## 4. የጥናቱ ውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው፡፡ ይህንም አላማ ለማሳካት በአንድ መምህር በመማር ላይ የሚገኙ 5 ምድብ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በቀላል የዕጣ ንሞና ስልት ሶስት ምድብ ተማሪዎች ተለይተዋል፡፡ በመቀጠል 3ቱ ምድቦች ቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲፈተኑ ከተደረገ በኋላ፣ ተቀራራቢ አማካይ ውጤት ያስመዘገቡ ሁለት ምድብ ተማሪዎች በተራ የዕጣ ንሞና ስልት አንዱ የሙከራ ሌላኛው የቁጥጥር ቡድን ተብለው ተሰይመዋል፡፡ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳላቸው የበለጠ ለማረጋገጥ በባዕድ ናሙና ቲቴስት ተሰልቷል፡፡

ሰንጠረዥ 1. የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት

| | ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የቲ-ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የባለሁለት ጫፍ ጉልህነት ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | የቁጥጥር | 49 | 29.42 | 5.83 | 0.273 | 97 | 0.78 |
| | የሙከራ | 50 | 29.72 | 4.72 | | | |

ሰንጠረዥ 1 እንደሚያመለክተው የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች 29.42 የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ 29.72 አማካይ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የአማካይ ልዩነት 0.3 ሲሆን፣ ይህም ልዩነት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ የተነሳ ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሊኖራቸው እንደሚችል ፍንጭ የሚሰጥ ነው፡፡ ነገር ግን አማካዩን ብቻ በማየት እኩል ናቸው ማለት ስለማይቻል ሌሎች ስታትስቲክስ ውጤቶችን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በ97 የነጻነት ደረጃ ተሰልቶ የተገኘው የቲ-ዋጋ 0.273 ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት ወደዜሮ የቀረበ መሆኑ ጉልህ ልዩነት እንደሌለ ፍንጭ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ቡድኖች የተመዘገቡት አማካዮች ተቀራራቢ መሆናቸው እንዲሁም የተመዘገበው የቲ-ዋጋ ወደ ዜሮ የቀረበ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤቱ ከ0.05 በላይ (0.78) ውጤት ተገኝቷል፡፡ ይህም ውጤት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በተፈተኑት ቅድመ ፈተና ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳላቸው ለማረጋገጥ አስችሏል፡፡

በሌላ በኩል የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ሰልጥነው የማንበብ ክሂልን ከተማሩ በኋላ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በብልሃቱ ሳይሰለጥኑ የማንበብን ክሂል ለአስር ክፍለጊዜያት ከተለማመዱ በኋላ ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ የሁለቱ ቡድኖች ድህረ

አንብቦ የመረዳት ትምህርት ፈተና በባዕድ ናሙና ቲቴስት ሲነጻር የተገኘውን ውጤት ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ 2. የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት

| ድህረ ፈተና | ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የቲ-ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የባለሁለት ጫፍ ጉልህነት ውጤት | የዝምድና ጥንካሬ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ | 50 | 31.60 | 4.57 | 2.055 | 97 | 0.043 | 0.20 |
| | የቁጥጥር | 49 | 29.84 | 3.93 | | | | |

ከሰንጠረዥ 2 መረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ድህረ ፈተና ካስመዘገበው አማካይ ውጤት 29.84 መደበኛ ልይይት 3.93፣ የሙከራ ቡድኑ ያስመዘገበው አማካይ ውጤት 31.60 መደበኛ ልይይት 4.57 በልጦ ይታያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ ቅድመ ፈተና ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት አንጻር የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት 31.60 በማምጣት ማሻሻልን ሲያሳይ፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 29.84 በማግኘት ቀድሞ ከነበረው አማካይ ላይ ጥቂት ለውጥ (0.42) ታይቶበታል፡፡ ከዚህ በመነሳት የቁጥጥር ቡድኑ በድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ለውጥ የተከሰተበት ምክንያት የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጊዜ ሂደት መሻሻል እንደሚያሳይ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል በሁለቱ ቡድኖች (በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኑ) መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር- አለመኖሩን ለማረጋገጥ የ ቲ ዋጋ እና የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህም መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የተገኘው የቲ ዋጋ 2.055 ሲሆን፣ የጉልህነት ደረጃው ደግሞ 0.043 ሆኗል፡፡ የቲ ዋጋ ከዜሮ በተወሰነ ደረጃ በመራቁ እና የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት ከ0.05 በታች በመሆኑ የተነሳ በሙከራ እና ቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንዳለ (ቲ(97) =2.05 P=0.043) ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዝምድና ጥንካሬ ደረጃው[1] 0.20 ሲሆን፣ ደረጃውም ደካማ ሊባል የሚችል ነው፡፡ በአጠቃላይ ከተገኘው የዝምድና ጥንካሬ በመነሳት የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል አስተዋጽኦ እንዳላቸው፣ የተጽዕኖው ደረጃ ግን ደካማ ተብሎ ሊገለጽ እንደሚችል የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

## 5. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በጥናቱ ቅድመ ፈተና በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች መካከል

[1] የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ Mujis (2004,139) Cohen (1988)ን ጠቅሰው እንደሚገልጹት የባለሁለት ጫፍ የP ዋጋ ከ0.05 በታች ከሆነ የሚሰላ ነው፡፡ የP ዋጋው ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ሲያመለክት፣ ኮኸንስ ዲ ደግሞ ከP ዋጋው በመነሳት የጉልህነት ደረጃውን ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት፡- ከ 0-0.20 = ደካማ፣ ከ0.21 እስከ 0.50 =መጠነኛ እንዲሁም ከ 0.51-1.00 መካከለኛ፣ ከ1.00 በላይ ጠንካራ የጉልህነት ደረጃን ይጠቁማል፡፡

ተቀራራቢ አማካይ ውጤት (የሙከራ ቡድኑ 29.72 የቁጥጥር ቡድኑ 29.42 አማካይ ውጤት) ተመዝግቦ ለአምስት ተከታታይ ሳምንታት (ለአስር ክፍለጊዜያት) ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ በማስተማር፣ ለቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ በክፍል ደረጃው በሚጠይቀው መደበኛ ሥርዐተትምህርት መሠረት (ጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ሳይማሩ) የማንበብ ክሂልን ከተማሩ በኋላ ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ተፈትነዋል። ሁለቱም ቡድኖች በድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲነጻጸር የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች 31.60 አማካይ ውጤት፣ 4.57 መደበኛ ልይይት፣ የቲ-ዋጋ 2.09 እና 0.042 የባለሁለት ጫፍ ጉልህነት ውጤት በማስመዝገብ ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ጉልህ ልዩነት አሳይተዋል። ይሁን እንጂ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተመዘገበውን ጉልህ ልዩነት መሰረት በማድረግ የዝምድና ጥንካሬ ሲፈተሽ 0.20 በመሆኑ ደካማ የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ አሳይቷል። ስለሆነም በሙከራ እና ቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ጉልህ ልዩነት የተመዘገበው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በጽሑፍ ውቅር ብልሃት የማንበብ ክሂልን በመማራቸው ምክንያት ነው። ይህ የተገኘው ውጤት ምን እንኳን ጉልህ ልዩነት ቢያሳይም የዝምድና ጥንካሬው ግን ደካማ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት ከቀደምት ጥናቶች መካከል Amiria et al. (2012)፣ ሙሉገበያ (2009)፣ እንድሪስ (2009) እና ጥሩነሽ (2005) የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ያሻሽላል ከሚሉ የጥናት ግኝቶቻቸው ጋር ተዛማጅነት ያለው ውጤት ተገኝቷል። ሆኖም Piyanukool (2001) የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች አሁን ላይ ማንበብን ለማስተማር ተግባር ላይ ከዋለው ዘዴ የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታን ከማሻሻል አኳያ የተለየ አስተዋጽኦ የለውም ከሚለው የጥናት ውጤት፤ እንዲሁም Ghafarpour et al. (2013) የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች የተማሪዎችን የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚጠይቁ ደረጃዎች ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሌላቸው በጥናታቸው ከገለጹት ጋር የተቃረነ ውጤት ተገኝቷል።

ከዚህ በተጨማሪ Adugnaw and Birhanu (2024) በማንበብ ትምህርት አውድ ውስጥ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን እና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማሻሻል ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሌለው ከጠቆሙት የጥናት ግኝት ጋር የተቃረነ ውጤት ተመዝግቧል። በሌላ መልኩ Williams et al. (2004) እና Williams and Pao (2011) በቅርብ ጊዜ እየተደረጉ ያሉ ጥናቶች በመካከለኛ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል እንደሚረዱ ከገለጹዋቸው የጥናት ውጤቶቻቸው ጋር ሲደጋገፍ፤ Englert and Thomas (1987) እና Mayer et al. (1980) ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ያላቸው ግንዛቤ የሚጨምረው እድሜያቸው ሲገፋ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ፣ ከወጣቶች ይበልጥ አዋቂዎች ይጠቅማሉ በሚል ካነሱት ንድፈ ሀሳባዊ እይታ አንጻር የተቃረነ ውጤት አሳይቷል። በአጠቃላይ በዚህ ጥናት የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል አስተዋጽኦ እንዳለው ለመረዳት ችሏል።

## 6. ማጠቃለያ እና አስተያየት

### 6.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነበር። ጥናቱ የባለሁለት ቡድን ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተናን መሰረት ያደረገ ከፊል ፍትነታዊ የተከተለ ሲሆን፤ ጎንደር ከተማ የሚገኘው ልዑል አለማየሁ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በአመቺ ንሞና ስልት ተመርጧል። በትምህርት ቤቱ በመማር ላይ የሚገኙ 2 ምድብ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ አንዱ የሙከራ፤ ሌላኛው የቁጥጥር ቡድን በመሆን በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል። በመቀጠል የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ በማስተማር ዘዴ፣ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በክፍል ደረጃው በሚጠይቀው መደበኛ ሥርዐተትምህርት መሠረት የማንበብ ክሂል ትምህርት ለ5 ሳምንታት ተምረዋል። ቅድመ እና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመሆን አገልግለዋል። በቅድመና በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና የተገኙ ውጤቶች በባዕድ ናሙና ቲቴስት ተተንትነዋል።

ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንዳመላከተው በቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ተመጣጣኝ አማካይ ውጤት የተስተዋለባቸው ቡድኖች በድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ጉልህ ልዩነት ታይቶባቸዋል። በመሆኑም፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ሲማሩ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ጉልህ አስተዋጽኦ አለው ወደሚል መደምደሚያ ተደርሷል።

### 6.2 አስተያየት

ከጥናቱ ግኝት በመነሳት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ በማንበብ ትምህርት አውድ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶችን በግልጽ ቢያስተምሩ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል አወንታዊ አስተዋጽኦ ይፈጥርላቸዋል። በዚህም ሂደት ተማሪዎቹ የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶቹን በተደጋጋሚ እንዲጠቀሙባቸው እድል መፍጠር ከመምህራኑ የሚጠበቅ ተግባር ነው። በሌላ በኩል የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች መተግበር ያለባቸው በአዎቂዎች እና በመካከለኛ የክፍል ደረጃዎች ነው የሚሉ የተለያዩ ክርክሮች ስላሉ፣ እነዚህን መነሻ በማድረግ በየትኛው የተሻለ ሊሆን እንደሚችል በይበልጥ ለመረዳት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ላይ ተመስርተው ተመራማሪዎች ጥናት ቢያደርጉ፣ ለሚነሱ ክርክሮች ግብአት በመሆን የተሻለ የማንበብ ትምህርት አውድ ለመፍጠር አመቺ እንደሚሆን አጥኚዎቹ ያምናሉ።

### ምስጋና

መረጃ በመስጠት ለተባበሩን ለልዑል አለማየሁ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደር እና ተማሪዎች ልዩ ምስጋና እናቀርባለን። ከፊል ሙከራዊ ጥናቱንም በመተግበር ለተባበሩንም መምህርት ምስጋናችን የላቀ ነው። ጎንደር ዩኒቨርሲቲም መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንድንችል ዘንድ የድጋፍ ደብዳቤ ስለጻፈልን እናመሰግናለን።

## 7. ዋቢ ጽሑፎች


ሙሉገበያ ያለው። (2009)። ''የጽሑፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፤ በአዲስ ዘመን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት'' አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት።

እንድሪስ አባይ። (2009)። ''በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በአማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ፤ በስድስተኛ ክፍል ተተኳሪነት።'' አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት።

ጥሩነሽ ክንፈ። (2005)። ''በሰሜን ሸዋ ዞን በእነዋሪ ሚሊኒዬም መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቴክስት አወቃቀር እውቀት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና።'' ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

ዘውዱ መብሬ። (2006)። ሚና ለዋጭ ዘዴ (Recipocal Teaching) የአማርኛ አፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትን ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋጽኦ፡- በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት።

Adugnaw, and Birhanu, S. (2024). Effects of Explicit Reading Strategy Instruction on Students' Reading Comprehension and Motivation: Grade 11 in Focus. *Ethiopian Renaissance Journal of Social Sciences and the Humanities, 11*(1).

Amare, T. (2024). The Relationship between Students Reading Strategy Use and Reading Comprehension among Ethiopian Secondary School Learners. *The International Journal of Humanities Education* 23 (1), 49-68.

Amiria, F., Zainalb, Z., & Samadc, A. A. (2012). Comprehension Performance. *Procedia-Social and Behavioral Sciences*, *66*, 402-409.

Brown, H. D. (1994). *Principles of Language Learning and Teaching: A course in Second Language Acquisition*. Pearson.

Early Grade Reading Assessment. (2010). *Ethiopian early grade reading assessment: Data analytic report: Language & early learning*. Addis Ababa (USAID/Ethiopia).

Englert, C. S., & Thomas, C. C. (1987). Sensitivity to text structure in reading and writing: A comparison between learning disabled and non-learning disabled students. *Learning Disability Quarterly*, *10*(2), 93-105.

Ghafarpour, H., Dehaghani, M. V., & Mahmoodi, A. (2013). Method effects on reading comprehension test performance: Text structure. *Life Science Journal*, *10*(4s), 436-441.

Lin, L. F. (2010). Senior high school students' reading comprehension of graded readers. *Journal of Language Teaching and Research*, *1*(1), 20-28.

Meyer, B. J. (1975). *The organization of prose and its effects on memory* (Vol. 1). Amsterdam; Oxford: North-Holland Publishing Company.

Meyer, B. J., & Ray, M. N. (2011). Structure strategy interventions: Increasing reading comprehension of expository text. *International electronic journal of elementary education*, *4*(1), 127-152.

Meyer, B. J., Brandt, D. M., & Bluth, G. J. (1980). Use of top-level structure in text: Key for reading comprehension of ninth-grade students. *Reading research quarterly*, 16(1),72-103.

Muijs, D. (2010). *Doing quantitative research in education with SPSS*. Sage.

O'Malley, J. M., & Chamot, A. U. (1990). *Learning strategies in second language acquisition.* Cambridge: C.U.P.

Oxford, R. L. (1990). *Language Learning Strategies: What Every Teacher Should Know.* Heinle & Heinle Publishers.

Piyanukool, S. (2001). Effects of teaching reading through* discussion of text structures. University of North Texas. Dotorial Dissertation.

Rose, H. (2012). Language learning strategy research: Where do we go from here?. *Studies in Self-Access Learning Journal*, *3*(2), 137-148.

Rubin, J. (1975). What the" good language learner" can teach us. *TESOL quarterly*, 41-51.

Vann, R.J. and Abraham, R.G. (1990). Strategies of Un-successful Language Learners. *TESOL Quarterly*, 24, 177-198.

Williams, J. P., & Pao, L. S. (2014). Developing a new intervention to teach text structure at the elementary level.

Williams, P., Hall, M., & Lauer, D. (2004). Teaching expository text structure to young at-risk learners: Building the basics of comprehension instruction. *Exceptionality*, *12*(3), 129-144.

Williams, M. and Burden, R. (1997). P*sychology for Language Teachers: A Social Constructivist Approach*. Cambridge: C.U.P.